# መለስ ቢያልፉም የተሰዉለት የህዳሴ ጉዞ ቀጥሏል

**መሐመድ ናስር** 08/19/13

ከኢትዮያዊያ አልፎ በመላው አፍሪካ የህዳሴ ጉዞ ውስጥ ሁነኛ ሚና የተጫወቱት የቀድሞ መሪያችን መለስ ዜናዊ ካለፉ እነሆ አንድ ዓመት ደፈነ፡፡ የመለስ ህልፈት መርር ዜና በተሰማበት ባለፈው ዓመት በዚህ ወቅትና በተከታዮቹ ጥቂት ወራት በአገርና ከአገር ውጭ ባሉ ጥቂት የፖለቲካ ቡድኖች ይደመጡ የነበሩት ክፉ ሟርቶች አያሌ እንደነበሩ የብዙዎቻችን የቅርብ ጊዜ ትዝታዎች ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡

እነዚህ አካላት መለስ የጤና ችግር ገጠማቸው ከተባለበት ጊዜ አንስቶ በሚያመቻቸው መንገድ ሁሉ በአገሪቱና ሕዝቦቿ ውስጥ አደገኛ የሆነ የጥፋት ሰብከትን አካሂደዋል፡፡ የመለስን ህልፈት በመመኘት ኢትዮጵያ በእሳት ማእበል እንድትናጥ፣ በብጥብጥና ሁከት እንድትታመስ አልመዋል፡፡ ስልጣን እጃቸው ላይ የወደቀች ያህል ተሰምቷቸው ብዙ ባክነዋል፤ ሌት ተቀን የሚዋትቱላት ስልጣን የቀረበቻቸው መስሏቸው እንቅልፍ አጥተው ቋምጠዋል፡፡

የመለስ ስርዓተ ቀብር እንኳ ሳይፈጸም አገሪቱን በተቃውሞና በሁከት ያምሳታል ተብሎ የተዘበከው ህዝብ ለክስተቱ የሰጠው ምላሽና ለመሪው ያሳየው ክብር፣ ያንጸባረቀው ሀዘን እና ያስተጋባው ወገንተኝነት ግን በእነዚህ የጥፋት ኃይሎች ለስልጣን የቋመጠ የጋለ ስሜት ላይ የቀዘቀዘ ውሃ በመቸለስ ለሃፍረት የሚያድርግ እንደነበር ብዙዎቻችን አንዘነጋውም፡፡

የመለስ ስርዓተ ቀብር ከአገር አልፎ ዓለም አቀፋዊ ክብርና ሞገስን በተላበሰ መልኩ ከተፈጸመ በኋላም ቢሆን እነዚህ አካላት የጥፋት ተግባራቸውን በተቀናጀ መንገድ ገፍተውበት ነበር፡፡ ሰዎቹ የመለስ ህልፈትን በመጠቀም በመቻቻልና በመፈቃቀድ የታጠረውን የኢትዮጵያ አንድነት በማፍረስ የሚፈጠረውን ቀዳዳ ተጠቅመው ዝንተ ዓለም የሚመኙትን ስልጣን ለመያዝ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ጥቂት የውጭ ተባባሪዎቻቸውን ከጎናቸው በማሰለፍ በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ አንዳንድ አገራት የተነሳውን ዓይነት ህዝባዊ አመፅ ለኢትዮጵያም ተመኝተዋል፡፡ ከመመኘትም አልፈው ህዝባችን በነውጥ እንዲተረማመስ የተቻላቸውን ሁሉ አሲራዋል፡፡

ሆኖም ግን መለስ ካለፉ በኋላ አገሪቱ ወደከፋ ብጥብጥና መፈረካከስ ውስጥ ትገባለች የሚለውን ጨምሮ መላውን የአገሪቱ ህዝብን ለስጋት ሊዳርጉ ይችሉ ከነበሩት አያሌ ክፉ ሟርቶች ውስጥ አንዱንም እንኳ ሳናስተናግድ እነሆ አንድ ዓመት አሳለፍን፡፡

ለዚህ ዓይነቱ ባዶ ሟርት ጆሮውን የነፈገው መላው የኢትዮያዊያ ህዝብ ባለፈው ዓመት ለሁለት ሳምንታት ያህል በዘለቀው ይፋዊ የሀዘን ጊዜ ውስጥ የእኚህን ታላቅ የአገር ልጅ ራእይና የህዳሴ ጉዞ ለማሳካት ከመቼውም በላቀ መልኩ ለመተግበር የገባውን ቃል ኪዳን በተግባር በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡

ህዝቡ ከዜናች ቀርቶ ከጠላት እንኳ ለማይጠበቀው የጥፋት ፕሮፓጋንዳ ጆሮውን በመንፈግና የሚያስደንቅ ንቀቱን በማሳየት ከመንግስት ጎን በመሰለፉ በአገሪቱ የተጀመረው የልማትና የእድገት ጉዞ ያለምንም ሳንካ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡ የመለስን እግር ተክተው አገሪቱን በመምራት ላይ የሚገኙት ባለስልጣናትም የመለስን ራእይና የህዳሴ ጉዞ በተፋጠነና በተሳካ መንገድ ለማስቀጠል የገቡትን ቃል ኪዳን በትጋት በመተግበራቸው የተጀመረው የለውጥ ሂደት ተቀጣጥሏል፡፡

ከዚህ አኳያ የመለስ ጉልህ አሻራ የሚታይበትን የእድገትና ለውጥ የልማት እቅድ ማንሳት ይቻላል፡፡ በአብዛኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫንና የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎችን ጨምሮ በዚህ ብሄራዊ የልማት ውጥን ውስጥ የተጠቀሱት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ያለፈው ዓመት ትግበራን ማንሳት ይቻላል፡፡ በህዝብ ቀጥተኛ ድጋፍ ጭምር የሚገነባው ታላቁ የኢትዮያዊያ ህዳሴ የኃይል ማመንጫ ግድብ በአሁኑ ወቅት ከ20 በመቶ በላይ ስራው ተጠናቋል፡፡ በእቅዱ ውስጥ ሊገነቡ ከታሰቡት 11 ያህል ትላልቅ የስኳር ፋብሪካዎች መካከል ስድስት ያህሉ በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውም ጉዞው በተፋጠነ መንገድ መቀጠሉን ለማሳየት የሚያስችሉ ማረጋገጫዎች ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በአገሪቱ ዘመናዊ የትራንስፖርት ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ሊቸረው የሚችለው የአዲስ አበባ ከተማ የባቡር ትራንስፖርት ግንባታ ስራ በተያዘለው እቅድ መሰረት እየተፋጠነ መሆኑም ሊጠቀስ የሚችል ሌላው ስኬት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ በተለያዩ ዘርፎች

በዚህ ብሄራዊ የልማት እቅድ ውስጥ የተካተቱት ተግባራትም በተሳካ ሁኔታ እየተከናወኑ መሆኑን በተጨባጭ እያየን ነው፡፡ ይህ አገራዊ የልማት እቅድ በእስካሁኑ ትግበራው ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚልቅ አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠርም የዜጎችን የገቢ ሁኔታ በማሻሻል ላይ መሆኑም ከተለያዩ ሪፖርቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ከመለስ ህልፈት በፊት ከነበሩት ዓመታት ጀምሮ በአገሪቱ እየተገነባ ያለው ኢኮኖሚ አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊና ያልተጠበቁ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ሳቢያ የአገራችንን ኢኮኖሚና የዜጎችን ኑሮ  ሲፈታተብ የቆየው የግሽበት ሁኔታም በተለይ ባለፈው ዓመት እጅግ ወርዶ ወደአንድ አሃዝ እንዲወርድ መቻሉም የመለስ ራእይና የህዳሴ ጉዞ በተፈለገው መልኩ እየቀጠለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

መለስ ከአገራቸው አልፈው ለአፍሪካ ብሎም ለመላው ዓለም በተቻላቸው መጠን ሁሉ የተጉለት ሰላምን፣ እድገትንና ጠንካራ ትብብርን የመፍጠር ተቆርቋሪነትና የሌት ተቀን ህልምና በተተኪዎቹ የአገሪቱ መሪዎች ተጠናክሮ መቀጠሉም ሌላው ሊታወስ የሚገባው ተግባር ነው፡፡

የመለስ ህልፈትን ተከትሎ ታላላቅ አገራት መሪዎችን ጨምሮ በመላው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ  መለስ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም በአፍሪካ ሰላም፣ ዴሞክራሲና እድገት እንዲመጣ ያደረጓቸውን ጥረቶች አዲሶቹ መሪዎችን እንዲገፉበት ያስተላለፉት አደራ ተጠብቆ ቀጥሏል፡፡ ይህ ለመለስ የተሰጠው እውቅና ዜጎችን ያኮራና አገሪቱንም በዓለም መድረኮች ያስጠራ ከመሆኑ ጋር ይህ የመለስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በአዲሶቹ መሪዎቻችን ተጠናክሮ መቀጠሉን እየታዘብን ነው፡፡ አገራችን አሁንም በሶማሊያ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ፤ የአገሪቱ ዜጎች ህይወትም እንዲሻሻል የበኩሏን ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ በሱዳንና በሌሎችም ችግር ባሉባቸው የአፍሪካ አገራት ውስጥ ሰላም ለማምጣት በመለስ የስልጣን ዘመን የተጀመሩት ጥረቶች አሁንም ቀጥለዋል፡፡

መለስ ካለፉ ልክ አንድ ዓመት ሞላው፡፡ መላው የኢትዮያዊያ ህዝብ የሙት ዓመታቸውን  በተለያዩ ክዋኔዎች መዘከር ጀምረዋል፡፡ ይህ ወቅት በተለይ አገሪቱን ለዝንት ዓለም ጨለማ ዳርጓት የነበረውን የተፈጥሮ ሁኔታ መልሶ ከመገንባት ባሻገር ይህንኑ የተፈጥሮ ኃብት የአገራዊው የህዳሴ ጉዞ ሞተር አድርጎ ሊጠቀም በሚያልመውና አረንጓዴ ልማት የተሰኘውን የመለስ ራእይ ከግብ ማድረስን ቁልፍ ግቡ አድርጓል፡፡

ከዚህ የመለስ ራእይ ጋር በተያያዘ ባለፉት ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በመላው አገሪቱ ከ20 ሚሊዮን ሄክራት የሚልቅ የተጎሳቆለና የወደመ የተፈጥሮ ኃብትን መልሶ የማልማትና የመጠበቅ ሰፊ ስራ መከናወኑን የተለያዩ መረጃዎች አረጋግጠዋል፡፡ ከዚሁ የተፈጥሮ ኃብት ልማትና ጥበቃ ጋር በተያያዘም ባለፈው ዓመት ከሰባት ቢሊዮን በላይ የዛፍ ችግኝ በመላው የአገሪቱ ህዝብ ቀጥታ ተሳትፎ ተተክሏል፡፡ ከዚህ ውስጥም በአሁኑ ወቅት 70 በመቶ የሚሆነው ችግኝ ጸድቆ ጥበቃና ክትትል እየተደረገለት መሆኑም በባለሙያዎች እየተነገረ ነው፡፡

የመለስን ህልፈት አንደኛ ዓመት በምናከብርበት በአሁኑ ወቅትም ካለፈው ዓመት የማይተናነስ ችግር በመላው አገሪቱ ለመትከል የታሰበ ሲሆን ህዝቡ መለስን በማሰብ ካለፉት ወራቶች ጀምሮ ባካሄደው የችግኝ ተከላ እስካሁን 4 ነጥብ 7 ቢሊዮን አዲስ የዛፍ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ የአገሪቱን ምርትና ምርታማነት በማጠናከር የምግብ ማስትናን በአስተማማኝ ለማረጋገጥ እንደሚያግዝ የሚታመንበት ይህ የደን ልማት ከመለስ ህልፈት አንደኛ ዓመት ዝክር ክዋኔ ጋር በተያያዘ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ይህ የሚያሳየው ኢትዮያዊያወኑ መለስን እያሰቡ ያሉት የእርሳቸው ጉልህ አሻራ ያለበትን የዚህች ጥንታዊት አገር ህዳሴን ያለምንም ሳንካ ለማስቀጠልና መለስ ሌት ተቀን የደከሙላቸውን የተለያዩ የልማት ውጥኖች እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን መሆኑን ነው፡፡

ይህ ጉዞ እጅግ በሚያመረቃ መልኩ ቀጥሏል፡፡ የህዳሴው ጉዞ ኢትዮጵያ መጠሪያዋ የሆኑትን ድህነትና ልመና ታሪክ ማድረግን ያልማል፡፡ ድህነትና ልመና ቃላት እንጂ በተግባራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የማይታወቁ ይሆኑ ዘንድም ይተጋል፡፡ አያሌዎች ህይወታቸውን የገበሩለትና ታሪክ ሊረሳው የማይችል መስዋእትነት የተከፈለለት ይህ የመታደስ ጉዞ በህዝቡ ልብ ውስጥ ተተክሏል፡፡

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በተወሰዱት የህዳሴው እርምጃዎች ለዘመናት በቁማቸው ያንቀላፉ የነበሩ ነፍሶች ተነቃቅተዋል፤ መስራት እንደማይችሉ በማሰብ ሳይታሰሩ ታስረው የነበሩ ሚሊዮን እጆች በማያቋርጥ ስራ ተጠምደዋል፤ በአጠቃላይ በራእይ እጦት ሳቢያ ለብዙ ዘመናት ጥቅም ላይ ሳይውሉ የኖሩ የአገሪቱ የተፈጥሮ ኃብቶች የዜጎች ህይወት እስትንፋስ ለመሆን በቅተዋል፡፡

ያለፉት ዓመታት ስኬቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሪቱ መሪዎች ራእይ ላይ ከፍተኛ የሆነ መተማመንና ተስፋ እንዲፈጥር መሰረት ሆኗል፡፡  ሕዝቡ መለስን በማጣቱ በሐዘንና ቁጭት ቢንገበገብም የተጀመረውን ራእይ ይዞ ለማስቀጠል ከልብ የመነጨ ስሜት ገንብቷል፡፡  እናም ይህ የእነመለስ ራእይ በአገሪቱ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ብቻ ሳይሆን በዜጎች ልብ ውስጥም የመታደስ መንፈስን ፈጥሯል፡፡ አዲስ ኃይልና ወኔም ሆኗል፡፡

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ያሉ ታዛቢያዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደሚገልፁት በአሁኑ ወቅት በመላው አገሪቱ ለሚታየው በመቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነት፣ ሰላምና መረጋጋት እንደዚሁም የሚያስደምም ኢኮኖሚያዊ እድገት እውን መሆን መለስና የስራ ባልደረቦቻቸው ያመነጩት ፌደራላዊው ስርዓት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡

ይህ የብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን ሁለንተናዊ እኩለነት፣ የስልጣን ባለቤትነትና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠው የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት እንዲተከል ዋነኛውን ሚና የተጫወቱት ደግሞ የነፃነት ትግሉን መንገድ በድፍረት የከፈቱትና በመንገዱ ላይ እስከህይወት ጭምር መስዋእትነት የከፈሉት መለስን ጨምሮ አያሌ ታጋይ የአገሪቱ ልጆች ናቸው፡፡

መላው የኢትዮጵያ ህዝብም የአሁኗ ኢትዮጵያ እውን እንድትሆን የተከፈለውን እጅግ ከፍተኛ መስዋእትነት ጠንቅቆ ይረዳል፡፡ በዴሞክራሲም ሆነ በኢኮኖሚ ግንባታው ረገድ የተወሰዱትን እርምጃዎች ተከትሎ የተገኘውን መልካም ውጤትም ማጣጣም ጀምሯል፡፡ በመሆኑም የዚህን የለውጥ ሂደት መጨረሻ ለማየት ከምንም በላይ ይጓጓል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ የመለስ ህልፈት በተሰማበትና ስርዓተ ቀብራቸውም በተፈጸመበት ወቅት ባሳየው መሪር ሀዘን ወቅት የገባውን ቃል ኪዳን የመለስን ህልፈት አንደኛ ዓመት ዚዘክር በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ አሁንም ድረስ በብዙ መልኩ ለሚሰበከው ሟርት ፍጹም ቦታ ሳይሰጥ የህዳሴ ጉዞውን ገፍቶበታል፡፡

እላይ ካወሳሁት እውነታ አኳያም በመለስ አመራር የተወጠነው የልማትና የለውጥ መንገድ በተሳካ ሁኔታ ጎዞውን ቀጥሏል፡፡ የአገሪቱ የፖለቲካ ሰዎችም የተጀመረው የህዳሴ ጉዞ እንዲቀጥልና ጫፍ እንዲደርስ ፍፁም የሆነ ህልምን ያነገቡ ናቸው፡፡ እነዚህ የአገሪቱ

መሪዎች በአሁኑ ወቅት በህዝቡ ውስጥ የሚንቀለቀለውን የለውጥ ፍላጎት ከማንም በላይ የሚገነዘቡ በመሆናቸው ኃላፊነታቸውን በላቀ ደረጃ ለመወጣት ሌት ተቀን እየደከሙ ስለመሆናቸው ያለፈው አንድ ዓመት ድካማቸው ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፡፡